የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ህግ ተማሪዎች ማህበር

HULSA

Hawassa University Law Students Association

የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ህግ ተማሪዎች ማህበር አምሳለ ፍርድ ቤት (MOOT COURT) ውድድር ለማድረግ የቀረበ ፕሮፖዛል

መጋቢት 2016 ዓ.ም

መግቢያ

የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪዎች ማህበር በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ አሁን እየተማሩ ያሉ እንዲሁም ተመርቀው የወጡ የህግ ተማሪዎችን ለማስተሳሰር እና እርስ በእርስ ያለውን አብሮነትን ለማጠንከር በተጨማሪም ተማሪዎች በህግ ትምህርት ዙሪያ ያላቸውን እውቀት እንዲያካፍሉ እንዲሁም እራሳቸውን እየፈተኑ በህግ እውቀት እንዲበለፅጉ እና ወደፊትም ብቁ የሆኑ የህግ ባለሙያዎችን ለማፍራት እየሰራ ያለ ማህበር መሆኑ ይታወቃል። ከዚህም አለፍ ሲል ለማህበረሰቡ ነፃ የህግ ድጋፍ ከድርጅቶች ጋር በመሆን እጅግ ጉልህ ሚና እየተወጣ ያለ ማህበር ነው።

ከሰራቸው ስራዎች መካከል ነፃ የህግ ድጋፍ , ነፅሁፍ ውድድር(Essay competition) ለተማሪዎች tutorial ዝግጅቶን በማዘጋጀት ተማሪዎች እርስ በእርስ ከመረዳዳት አልፈው ለፈተናቸው ብቁ ይሆኑ ዘንድ የበኩሉን አስተዋፆ አበርክቷል እንዲሁም ከዚህ ቀደም ለሁለት ዙር ምስለ ፍርድ ቤት ውድድር በማድረግ በተማሪዎች እጅግ ከፍተኛ የመናገር እና የመፃፍ ችሎታቸውን ከማዳበር አልፎም የአለም አቀፍ ሚዲያ ማለትም ቢ.ኦ.ኤ(VOA) እንዲህም አገር አቀፍ ሚዲያ(ደቡብ ቲቪ) ሽፍኝ በማግኘት ማህበረሰቡን በማስተማር ደማቅ ስራ መስራቱ ይታወሳል።ከዚህም በተጨማሪ ከኢጋር አካላት ጋር በመሆን መጽህፍትን ለተማሪዎች ተደራሽ ይሆን ዘንድ ለህግ ትምህርት ቤት ማበርከቱ የማይዘነጋ ሀቅ ነው ።የጀመራቸውን መልካም ስራዎች ለማስቀጠል ትልቅ ፍላጎት እና መነሳሳት እንዳለው እያሳወቀ ይህንንም መሠረት አድርጎ በቀጣይ የ2016 ዓ.ም 3ኛው ዙር የ ማህበሩን የምስለ ችሎት ከኢጋር አካላት ጋር በመተባበር የሀምሳለ ፍርድ ቤት ውድድር ለህግ ተማሪዎችን ለማዘጋጀት እቅድ ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ።

<u>የ አምሳለ ፍርድ ቤት ውድድር አላማ</u>

በዩኒቨርስቲው የሚገኙ የህግ ተማሪዎች የተግባር ልምምድ ይረዳ ዘንድ ብሎም የህግ ትምህርት ቤቱን በተለያዩ የሀገር አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሀምሳለ ፍርድ ቤት ውድድር የሚወክሉ ተማሪዎች ያፈራ ዘንድ የህግ ትምህርት ቤት መምህራን እና አመራር አካላት የተማሪዎች አቅም ይፈትሹ ዘንድ በሚደረገው ጥረት ህግ ትምህርት ቤቱ የድርሻውን እንዲወጣ እና ተማሪዎችም የበኩላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ለማስቻል ሲሆን በዚህም የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪወችን ለ ቀጣይ ውድድሮች በማዘጋጀት እና ህግ ተምህርት ቤቱን ወክለው እነዲወዳደሩ በማድረግ ተማሪዎች የተሻለ ብቃት እንዲኖራቸው እንዲሁም ትምህርት ቤቱን እነዲያስጠሩ ያስችላል፡፡ በአጠቃላይ ይህ ውድድር የሚከተሉት ዋና ዋና አላማወቸ የኖሩታል፤

የህግ ተማሪዎች ውስጥ በተግባር የታገዘ እውቀት ይሠንቁ ዘንድ ማስቻል እና ተማሪወች በክፍል ውስጥ የማያገኙትን ቴክኒክ ለማስተማር ።

- ★ በሀገር አቀፍ እና አህጉር አቀፍ የሀምሳለ ፍርድ ቤት ውድድር ላይ የ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ትምህርት ቤት ብሎም አጠቃላይ ዩኒቨርስቲውን የሚያስጠሩ ተማሪዎችን ማፍራት ።
- ★ ማህበረሰቡን በተዘዋዋሪ ለማስተማር እና ግንዛቤ መፍጠር
- ★ ተማሪወች የመመራመር የመፃፍ እና ተናግሮ የማሳመን ክህሎታቸውን ለማሳደግና ተመልካቹ ላይ መነሳሳትን ለመፍጠር

- ★ ይህን መወዳደርያ መድረክ በመጠቀም ተማሪዎች ያሉበትን አሁናዊ ሁኔታ መፈተሽ እና ለቀጣይ ስራዎች ግብአት ማግኘት ።
- ★ ከአጋር ድርጅቶች በቀጣይነት ለመስራት የሚያስችል ግንኙነት መመሥረት
- ★ የተማሪዎች የጽሁፍ እንዲሁም የንግግር ችሎታ ማጎልበት ።

<u>ዋና አዘጋጅ</u>

ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪዎች ማህበር

<u>ተባባሪ አዘጋጅ</u>

ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት የ አምሳለ ፍርድ ቤት አስተባባሪ እና አጋር ድርጅቶች

<u>የፕሮግራሙ ስያሜ</u>

3ኛው HULSA አምሳለ ችሎት ውድድር

<u>ቦታ</u>

ምስለ ፍርድ ቤት አዳራሽ(Block 122)

<u>ቀን</u>

ሚያዝያ 10,11 2016 ዓ.ም(እንደሁኔታው ሊቀየር የሚችል)

<u>ሰዓት</u>

ጠዋት 2:30_6:00

ከሰአት 8:00_11:00

<u>የተሳታፊዎች ብዛት</u>

ከ 100 - 200 የሚደርሱ የሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ የህግ ተማሪዎች፣ የህግ ተማሪዎች መምህራን እና ተጋባዥ እንግዶች ።

<u>ተጋባዥ እንግዶች</u>

- ➢ የህግና ገቨርናንስ ኮሌጅ ዲን እና የትምህርት እና ምርምር ምክትል ዲን

- የህግ ትምህርት ቤት ሀላፊ እና መምህራን
- የፍርድ ቤት እንግዶች
- የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር አካላት
- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት
- የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ህብረት ፕሬዚዳንት እና የትምህርት እና ጥናት ሀላፊ
- ተባባሪ ድርጅት ሀላፊዎች ወይም ወኪሎቻቸው

<u>ተወዳዳሪ ብድኖች ብዛት እና አወቃቀር</u>

ይህ የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ሊደረግ የታቀደው በሁለት ዙር ሲሆን ይህ እውን ይህን ዘንድ 12 ተወዳዳሪ ብድኖች አስፈላጊ ናቸው ። እያንዳንዱ ብድን ሁለት ተማሪዎች የሚኖሩት ሲሆን የብድን አወቃቀሩም የሚሰራው የትምህርት ደረጃን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል ። ከነዚህ 12 ቡድኖች መካከል አራቱ ቡድን በፅሁፍ (Memorial)የሚወድቁ ይሆንና ቀሪወቹ በ 2 ቀን የፅሁፍና የቃል ክርክር አሸናፊዎች ይለያሉ።

<u>ዳኞች</u>

የህግ ትምህርት ቤቱ የሚጠቁማቸው የህግ አስተማሪዎች ወይም እንደ አስፈላጊነቱ እና የገንዘብ አቅም በዳኝነት እያገለገሉ ያሉ እንዲሁም ከዚህ ቀደም በምስለ ፍርድ ቤት ዳኝነት ልምድ ያካበቱ የህግ ባለሙያዎች ናቸው።

<u>የሁነቱ ክፍሎች ክፍሎች</u>

<u>ቀን አንድ የካቲት 10</u>

ጠዋት እስከ 2:00

የህግ ተማሪዎች እና ተጋባዥ እንግዶች በውድድር አዳራሽ ይገኛሉ ።

ጠዋት ከ2:00 እስከ 2:30

ጠዋት 2:30_5:00

በተመሳሳይ ሰአት የመጀመሪያ ዙር የጠዋት ፕርግራም የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ይካኼዳል

ከሰአት ከ8:00_11:00

በተመሳሳይ ሰአት የመጀመሪያ ዙር የከሰአት ፕሮግራም የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ይካኼዳል

<u>ቀን ሁለት የካቲት 11</u>

ጠዋት ከ2:30_5:00

የቀን ሁለት የጠዋት ፕሮግራም የምስለ ፍርድ ቤት ውድድር ይካኼዳል

ከሰአት ከ8:00_11:00 የካቲት 11

የመጨረሻ ዙር ውድድር የሚካኼድ ይሆናል

የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በ ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የህግ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ይደረጋል።

የመክፈቻ ንግግር በህግና ገቨርናንስ ኮሌጅ ወይም በህግ ትምህርት ቤት ዋና ሀላፊ የሚደረግ ይሆናል

ከ9:20_10:30 ሽልማት እና የፕሮግራም መዝጊያ የምስጋና መስጫ እና የሰርተፊኬት መርሀ ግብር ።

ምስጋናው ተመስገን -የህብረቱ ፕረዚዳንት